የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

መስከረም 30/2003

## የወይዘሪት ብርቱካን ሚዴቅሳን መፈታት አስመልክቶ የመለስ አገዛዝ ውግዘት ይገባዋል

ወይዘሪት ብርቱካን ከ 500 ቀናት በላይ በእስር ያሳለፈችው በበቀል የተዋጠው የመለስ አገዛዝ ህግን ጥሶ ስላሰራት መሆኑ የሚታወቅ ነው።በአሁኑ ወቅት ብርቱካንን ፈታሁ በሚል ይህ አገዛዝ ሊመጻደቅ መነሳቱንም እየታዝብን ነው። ወይዘሪት ብርቱካንንም በማስገደድና የሽማግሌ ኮሚቴ የሚባሉትን አገልጋዮቹን በመጠቀም ያስፈረማት የይቅርታ መጠየቂያ ሰነድ የዚህን አፋኝ አገዛዝ ህገወጥነት የሚያረጋግጥ ነው።

የመለስ አገዛዝ ክ 35 ሺ ያላነሱ ዜጎችን በየማጎሪያው እያስቃይ ያለ መሆኑና ከ1985 ጀምሮ እነ አበራሽ በርታን፤ ከ1983 ጀምሮ ደግም እነ ጸጋዬ ገብረመድህንን አፍኖ ደብዛቸውን ማጥፋቱ ሊዘነጋ አይገባውም። አንድዋ ዜጋ ስትፈታ ሺዎች ገና እየማቀቁ መሆናችውን የመለስ አገዛዝ ሊያረሳሳን አይገባውም። አስገድዶ ማስፈረም የሚያጋልጠው አገዛዙን እንጂ ፈራሚውን/ፈራሚዋን ባለመሆኑ ይህን በተመለክተ ግምትንም ማስተካከል ተገቢ ይሆናል። ወይዘሪት ብርቱካን መፈታትዋ ለቤተሰብና ወዳጅ ሁሉ አስደሳች ዜና መሆኑ እንዳለ ሆኖ የዜጎች ዋና ተልዕኮና ትኩረት በቀሩት ሺዎች መፈታት ላይ መሆን አለበት። በየማጎሪያው ታፍነው ያሉ ዜጎች ሁሉ የሁላችንም ወገኖች ናቸውናም ልዩነት ሳናደርግ እንዲፈቱ ልንጮህላቸው ይገባል። የሰብዓዊ መብት መከበር ጥያቄ ሁሉን አቀፍ መሆኑ መሰረታዊ መሆኑንም መርሳት አይኖርብንም።

በመሆኑም ኢፖእአኮ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች እስኪፈቱ ድረስ ትግላችን ይቀጥል እያለ የመለስ አገዛዝ በወይዘሪት ብርቱካን መፈታት ዙሪያ ሊያደናግር እየጣረ ያለውን ማክሸፍ ያስፈልጋል ይላል።

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE